# ጥንተ አብሶ እና ተዋሕዶ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!

በነገረ ሃይማኖት ውስጥ እስከ አሁን ድረስ ሆኖ እንዳየነው፣ እንደሚታወቀው፣ እየሆነም እንደምናየው ከባለቤቱ ከመድኃኔዓለም ክርስቶስ አንሥቶ መትሕተ ፈጣሪ መልዕልተ ፍጡራን በሆነችው በቅድስት ድንግል ጽዮን ማርያም፣ በቅዱሳን መላእክት፣ በአበው ጻድቃን ሰማዕታት /ቅዱሳን/ በሁሉም ላይ ክህደት ወይም ኑፋቄ ያልተነሣበት ማንም የለም፡፡ በወላዲተ አምላክ ላይ ከሚነሡ ኑፋቄዎች ሁሉ የከፋውና ከባዱ ኑፋቄ ደግሞ ይህ ከላይ በርእስ የተጠቀሰው የኑፋቄ ወይም የክህደት ዓይነት ነው፡፡ ክህደት ወደነው አይመጣም በቦታና በጊዜም አይወሰንም፡፡ አሳች ሰይጣን እስካለ ጊዜ ድረስም ይቀጥላል፡፡ የሥጋ ሞት ለሰው ልጆች ሁል ጊዜ እንግዳ እንደሆነ ሁሉ የነፍስ ሞት ኑፋቄ ወይም ክህደት ደግሞ ሁል ጊዜ እንግዳ ነው፡፡

ምንም እንኳን ክህደት ወይም ኑፋቄ በየዓይነቱ እንደሚነሡ እንደሚመጡ ከክርስቶስ ጀምሮ ደቀ መዛሙርትም በወንጌልና በየመልእክቶቻቸው አስቀድመው ያስጠነቀቁና ያሳሰቡ ቢሆንም ጉዳዩ በቅዱሳት መጻሕፍት በግልጽ ይቀመጥም አይቀመጥ ኑፋቄ ወይም ክህደት ያልተነሣበት የጉዳይ ዓይነትም የለም፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ወይም መጽሐፍ ቅዱስ በቁሙ የምሥጢር መጽሐፍ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ሲናገርም በቀጥታ ግልጽ ባለ ቋንቋ ከመናገር ይልቅ በምሳሌ ማስረዳትን ይመርጣል፡፡ ወንጌልን ስናነብ ማለትም የጌታን ትምህርት ያየን እንደሆነ ያለ ምሳሌ ቅኔና ምሥጢር የተናገረው ቃል የለም ማለት ይቻላል፡፡ አስቀድሞ "አፌን በምሳሌ እከፍታለሁ" መዝ. 78፤2 ማቴ 13፤35 ተብሎ ተጽፏልና፡፡

ይህ ያነሣነው ርእሰ ጉዳይም እንደ ሌሎቹ ዋና ዋና ጉዳዮች ሁሉ በምሳሌ በቅኔ ተነግሮ ለማመኑ ከጆሮ ይልቅ ለልብ ከተተው ነገረ ሃይማኖቶች አንዱ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ ሰዎች ሲሰነካከሉበትና ሲወድቁበት ይታያል፡፡ ምንም ቢሆን ግን ቅንና ንጹሕ ልብ ያላቸው ሰዎች ምሥጢሩ የቱንም ያህል የተሠወረ ቢሆንም የተሠወረው ለሚጠፉት እንጂ ለሚድኑት አይደለምና በንጹሕና ቅን ልባቸው እየተመሩ ከመሠናከል ይድናሉ ይተርፋሉ፡፡ ጠማማውን ክፉውንና የድፍረቱን መንገድ ከመምረጥ ይታቀባሉ፡፡

አሁን ችግሩ ያለው ክፉ፣ ሐኬተኛ፣ ጠማማ፣ ዐመጸኛና ዕቡይ ልብ ባለው ሰው ላይ ነው፡፡ እንዲህ ዓይነት ልብ ያለው ሰው ደግሞ ምንም እንኳን ጉዳዩ በበቂ ደረጃ ሊገባ በሚችል አገላለጽ በግልጽ የተጻፈና የተነገረ ጉዳይ ቢሆንም

ጠማማ ሐኬተኛና ዐመፀኛ ልብ ያለው ሰው ከክፋቱና ከጥመቱ ከዐመፃውም የተነሣ ቀና ቀና ነገር አይታሰበውምና አማን በአማን ብሎ ለመቀበል ወይም ለማመን ይሳነዋል፡፡

ስለሆነም ጉዳዩ ያለው ነገረ ሃይማኖቱ በግልጽ በመጻፉና ባለመጻፉ ላይ ሳይሆን የልባችን ቀናነት ወይም ጠማማነት፣ ደግነት ወይም ክፉነት፣ ትሁትነት ወይም ዐመፀኛነት፣ አማኝነት ወይም ተጠራጣሪነት ላይ ነው ማለት ነው፡፡ ጻድቅ፣ ቅን፣ ትሑትና ንጹሕ ልብ ያለው ማንኛውም ክርስቲያን የተማረም ይሁን ያልተማረ እንኳንና በወላዲተ አምላክ ላይ ይቅርና በማንም ሰው ላይ የሚያጎድፍ የሚያረክስ ነገር ማድረግ አይቻለውም፡፡ ክፉ ዐመፀኛና ጠማማ ልብ ያለው ሰው ደግሞ እንኳንና ቅዱሳኑን ባለቤቱን ልዑል እግዚብሔርን ባልተገባ ሁኔታ ከመዝለፍ፣ ከመንቀፍ፣ ከመተቸት ጨርሶም ከመካድ ወደ ኋላ እንደማይል ታዝበናል ተመልክተናልም፡፡

አሁን ለዚህ ኑፋቄ በተለመደው መንገድ እንጴ! ምን ነው? ጠቢቡ ሰሎሞን መኃ.4፥12 "ወዳጄ ሆይ ሁለንተናሽ ውብ ነው ነውርም የለብሽም!" በማለት በሙኀልየ ሙኀልይ ወይም የመዝሙሮች መዝሙር በሆነው መዝሙሩ እንዲያ ያወደሳትና ያመሰገናት ማንን ሆነና?፣ ንጽሕናዋን ሲናገር አይደለም ወይ?፤ ጥንተ አብሶ ወይም የውርስ ኃጢአት እንደሌለባት ሲናገር አይደለም ወይ? እሺ ይሄ ማለት ካልሆነ ሌላ ታዲያ ምን ማለት ነው? ቀጥሎም "እኅቴ ሙሽራዬ የተቆለፈ ገነት የተዘጋ ምንጭ የታተመ ፈሳሽ ናት" መኃ. 4፥7 ብሎ ያወደሳት ማንን ሆነና? ኧረ ለመሆኑ ከአምላክ እናት በላይ ማን ኖሮ ጠቢቡ ለሌላ ለማን እንዲህ ዓይነት ቅኔና መዝሙር ይቀኛልና ነው ለእሷ እንዳልሆነ የምታስቡት? እሺ ለእሷ ካልሆነ በሉ ሌላ ማን የተገባው ኖሮ ይሄ ቃል ለማን ተነገረ? ጥቀሱልን?

ልበ አምላክ ዳዊትም በመዝ.44፥9 ላይ "በወርቅ ልብስ ተጎናጽፋ ንግሥቲቱ በቀኝህ ትቆማለች፤ ልጄ ሆይ ስሚ እዪ ጆሮሽንም አዘንብይ፤ ወገንሽንም የአባትሽንም ቤት እርሺ፤ ንጉሥ ውበትሽን ወዷልና፤ እርሱ ጌታሽ ነውና" ብሎ ስለ ድንግል ስለ ወላዲተ አምላክ ከተናገረው ጥቅስ ላይ "ወገንሽን የአባትሽንም ቤት እርሺ" ማለቱ ምን ማለት ነው?፡፡ ይሄን ማለቱ እኮ አንቺ ከወገኖችሽ የተለየሽ ነሽ ወይም ከአዳምና ከሔዋን ጀምሮ በዘር የሚተላለፈው የውርስ ኃጢአት ወይም ጥንተ አብሶ የለብሽም ከዚያ ጠብቆሻል፣ ለይቶሻል ፣ አንጽቶሻል (ከጉድፈት በኋላ ሳይሆን ሳትጎድፍ አስቀድሞ ከመጉደፍ አነጻት)፣ ሰውሮሻል፣ ታድጎሻል፣ ማለቱ አይደለምን? ይሄን ማለቱ ካልሆነ ወገንሽን የአባትሽንም ቤት እርሺ ማለት ታዲያ ምን ማለት ነው?

እንዲህ ዓይነቱን ምሥጢር መረዳት ካልቻላቹህማ ምኑን የእግዚአብሔርን ቃል(መጽሐፍ ቅዱስን) ተረዳቹሁት? ቃሉስ ምኑን ሕይወት ሆናቹህ? እያልኩ መልስ ከመስጠት ይልቅ ምንም እንኳ ቃሉ ማለዳ ማለዳ ሁሌም አዲስ ቢሆንም ትንሽ ለየት ባለ መንገድ ነገሩን ለማሳየት መሞከሩን መርጫለሁ፡፡

ይህ ኑፋቄ ያለባቸው ሰዎች በአምላክ እናት ላይ ጥንተ አብሶ ስለመኖሩ የሚናገር ወይም የሚያረጋግጥላቸው ጥቅስ ከመጽሐፍ ቅዱስ አንዲትም እንኳ አይጠቅሱም እንዲያው በጥቅሉ የሰው ልጆች ያ የውርስ ኃጢአት እንደነበረብን የሚናገሩትን ጥቅሶች በመጥቀስ "እሷም የሰው ልጅ ናትና ከዚህ የተለየች ልትሆን አትችልም!" ይላሉ እንጅ፡፡ እንዲህ ማለታቸው ጌታም በሰው ልጅነቱ ጥንተ አብሶ አለበት ማለታቸው እንደሆነ አልገባቸውም፡፡ በጣም የሚገርመው ነገር እውነቱ እንዲህ በሆነበት ሁኔታ ከየት አምጥተው የአምላክን እናት ጥንተ አብሶ አለባት እንደሚሉ ነው፡፡ ያው ቀደም ሲል እንደገለጽኩት ከእኪተኛው ልቦናቸው አፍልቀው መሆኑ ነው፡፡

እንደዚህ ዓይነት ኑፋቄ ያለባቸው ሰዎች የሚጠቅሱት አንድ ሌላ ቃል አለ ሳይገባቸውና ተሠውሮባቸው፡፡ እሱ ምንድ ነው? ቅዱስ ያሬድ በድርሰቱ "አንጺሖ ሥጋሀ ኀደረ ላዕሌሃ፤ ሥጋዋን አንጽቶ አደረባት ብሏል እና ይሄን ማለቱ ጥንተ አብሶ ነበረባት ማለቱ ነው" ብለው ለራሳቸው በመተርጎም የክሕደት ማጥ ውስጥ ተነከሩ፡፡ እውነቱ ግን እንዲህ አይደለም፡፡

ልዑል እግዚአብሔር የሰውን ልጅ የፈጠረ አንድ ጊዜ ነው፡፡ እሱም አዳምን በፈጠረባት ጊዜ፤ አባታችን አዳምን ከአራቱ ባሕርያተ ሥጋና ከሦስቱ ባሕርያተ ነፍስ ፈጥሮታል፡፡ ከዚያ በኋላ ግን ሔዋንን ከአጥንቱ ከአዳም አጥንት፤ ሌሎቻችንን ደግሞ ከአብራኩ ከአዳም አብራክ፤ ከሔዋን ማሕፀን በከሂሎቱ በፈቃዱ እያዋለደ አራብቶናል (ፈጥሮናል)

ከአዳም ሌላ ማለትም ከአዳም ውጭ ከላይ ከገለጽኩት መንገድ ውጭ የፈጠረው የሰው ዘር የለም፡፡ ሁሉም የለበሰው የአዳምን ሥጋ ነው፡፡ የአዳም ሥጋ ደግሞ ከድንግል ማርያም በስተቀር እስከ ክርስቶስ የመስቀል ሞት ድረስ ያለው የሰው ዘር በአዳም በደል ምክንያት ሁሉ የውርስ ኃጢአት የሠለጠነበት ነበር፡፡

ወላዲተ አምላክም የአዳም ልጅ እንደመሆኗ መጠን እንደ ሌሎቹ የአዳም ልጆች ሁሉ ያ የውርስ ኃጢአት ሊኖርባት ይችል ነበረና የአዳም ልጅ በመሆን ወይም ጥንተ አብሶ ያለበትን የአዳምን ዘር ሥጋ በመልበስ ወይም ከእርሱ ዘር በመወለድ ብቻ ከሚወረስ የውርስ ኃጢአት ወይም ጥንተ አብሶ አንጽቶ ወይም ጠብቆ ወይም ታድጎ ወይም አድኖ አደረባት ተወለደባት ለማለት "አንጺሖ" አለ እንጂ ሥጋዋ ያደፈ ሆኖ ኖሮ ያንን ያደፈውን አንጽቶ አደረባት ለማለት አልነበረም፡፡

አሁን ይህች ቃል "አንጺሖ" የምትለዋ ቃል ጥሩና እንዲህ ያለ ኑፋቄ ወይም ክህደት ካለባቸው ሰዎች ጋርም ልታግባባን ወይም ልታስታርቀን የምትችለው ቃልም እሷው ራሷ ናት፡፡ አንጺሖ ሲል አንጽቶ ማለቱ ነው፣ ትክክል ነው ያግባባናል፡፡ ቁም ነገሩ ያለውም እዚህ ላይ ነው፡፡ እንዳነጻት ካወቁ ልዑል እግዚአብሔር ንጹሕ አካሏን ፈልጎታል ሽቶታል ማለት ነው፡፡

ንጹሕ አካሏን ከፈለገው ማደፉን ካልወደደው ደግሞ ቀድሞውን እግዚአብሔር እንዲያድፍ ወይም እንዲጎድፍ የሚተወው እስኪያድፍ እስኪጎድፍ የሚጠብቀው ወይም የፈለገው ስለምንድን ነው? የአምላክ ከወላዲተ አምላክ መወለድ እንደ እንግዳ ደራሽ እንደ ውኃ ፈሳሽ እንዳልሆነ ይታወቃል፡፡ ዓለም ሳይፈጠር ገና በአምላክ ልቦና ታስባ ትኖር ነበርና ወይም ደግሞ በሰው ሰውኛው ገና ለአዳም "በአምስት ቀን ተኩል ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሀለሁ" ብሎ ቃል ኪዳን ከገባለት ጊዜ ጀምሮ ከእርሷ እንደሚወለድ የሚታወቅ ነገር ነበር፡፡

ይህ ማለት ደግሞ አምላክ ከድንግል የመወለዱ ነገር ድንገት የሆነ ነገር አይደለም ማለት ነው፡፡ በመሆኑም እግዚአብሔር ከድንግል መወለዱ በድንገት ካልሆነ ማደሪያውን በኋላ ሊያነጻት ነገር እስኪያድፍ እስኪጎድፍ የሚጠብቅበት ወይም የሚተወው ለምንድን ነው? ምን ምክንያት አለው? ማንጻቱ ካልቀረ ቀድሞውንም ገና ሳያድፍ ከማደፍ እንዳያነጻት ምን ይከለክለዋል? ምንም!!! በመሆኑም ከእርሷ እንደሚወለድ አስቀድሞ እንደማወቁ መጠን ማደሪያውን ሁለነገሯን አዘጋጅቶ፣ አሰናድቶና አንጽቶ ማለትም ቀድሞ ከነበረው ሰው በመሆን ብቻ ከሚታደፍበት ልማድ አንጽቶ ሰዓቱ ሲደርስ አድሮባታል ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስን ነስቶ ተወልዶባታል፡፡

ነቢየ እግዚአብሔር ኢሳይያስ 1፥9 "የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ዘርን ባያስቀርልን ኖሮ እንደ ሰዶም በሆንን እንደ ገሞራም በመሰልን ነበር!" ያለውም ለዚህ ነው፡፡ ከዚያ የውርስ ኃጢአት ነጻ የሆነች ወይም የነጻችና ለእርሱ ማደሪያነት የበቃች የተገባች ዘርን ባያስቀርልን ኖሮ ለአምላክ ማደሪያነት ያደፈና የጎደፈ ሰውነት አይሆንምና አይገባምና አይስማማውምና አምላክም አይወለድም ነበር፡፡ እርሱ ባይወለድ ኖሮ ደግሞ እጣ ፋንታችን ዕድል ተርታችን ሰዶምና ገሞራን መሆን ነበር፤ ማለቱ ነው፡፡ "ልዑል ማደሪያውን ቀደሰ" ያለው ቅዱስ ዳዊትም ከዚህ ተነሥቶ ነው፡፡ ከሰውነት እድፈት ለያት አከበራት ለማለት፡፡ መዝ.45፥4

በመሆኑም የአምላክ ሰው መሆን እንደ እንግዳ ደራሽ፣ እንደ ውኃ ፈሳሽ ካልሆነ፤ እግዚአብሔር በባሕርይው ንጹሕ ነውና ንጹሕ ነገርን ይወዳል ወይም ንጹሕ ነገርን ነው የሚወደው ካልን፤ እግዚአብሔር እንደፈጣሪነቱ በሁሉም ነገር ላይ ያሻውን ነገር የማድረግ ሥልጣን ኃይልና ችሎታ አለው ካልን ማለትም በአዳም ልጆች ላይ በዘር በሚተላለፈው በውርስ ኃጢአት ወይም በጥንተ አብሶ ላይ ጭምር ያሻውን የማድረግ ሥልጣን አለው ካልን፡፡ የድንግልን ሥጋ በኋላ ሊወለድባት ወይም ሊያድርባት ሲል ሊያነጻው ነገር እስኪያድፍ የሚጠብቅበት ምን ምክንያት አለው? አድፎ ከሚነጻ ሰውነት ይልቅ ከጅምሩ የነጻ ወይም ያላደፈ የተጠበቀ ሰውነት እንደሚሻለው ስለማያውቅ ወይም የሚሻለውን የማያውቅ ነው ማለታችው እንደሆነ ልብ ብለውት ይሆን?

ወይስ ልዑል እግዚአብሔር በጥንተ አብሶ ላይ ምንም የማድረግ ኃይልና ሥልጣን የለውም ማለታቸው ነው? እኛስ አምላካችን ስሙ ለዘለዓለም የከበረ የተመሰገነ ይሁንና ንጹሐ ባሕርይ እንደመሆኑ መጠን ፍጹም ንጹሕ የሆነ ነገርን ይወዳልና አሁንም ክብር ምስጋና ይግባውና ፍጹም ንጹሕ ቅዱስ አድርጎ ባዘጋጀው በድንግል ሥጋ ላይ ያደረ ወይም የተወለደ ነው፡፡ የእኛስ አምላካችን በውርስ ኃጢአት ወይም ጥንተ አብሶን ጨምሮ የሚቀር ነገር ሳይኖር በሁሉም ነገር ላይ ፍጹም ሥልጣን ያለው አምላክ ነው ያለን፡፡ እናቱ ቅድስት ድንግል ጽዮን ማርያምም ክብር ምስጋና ይግባትና የኛስ እናታችን ምንም ምክንያት እንከን የሌለባት ፍጹም ንጽሕት ቅድስት ብፅዕት ናት፡፡

የእነዚህ መናፍቃን መሰናከል ሌላኛው ምክንያት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በወንጌል ላይ የተናገረችውን ቃል ጨርሶ ካለመረዳትም ይመነጫል "መንፈሴም በአምላኬ በመድኃኒቴ ሐሴት ታደርጋለች" ሉቃ. 1፥47 ማለቷን ይጠቅሳሉ፡፡ ተናገርን እኮ! ልጇ ወይም አምላኳ በርግጥም መድኃኒቷ ነው፡፡

እንዴትና እንዲህ ያለችበትም ምክንያት ከጥንተ አብሶ አድኗታልና ነው፡፡ ከተያዘች ከጎደፈች በኋላ ሳይሆን ከመያዟ ከመጉደፏ በፊት የአዳም ልጅ በመሆኗ ብቻ ተጠቂ ልትሆን ትችል ከነበረችበት ችግር አንጽቷታልና ወይም ያነጻት እሱ ነውና ታድጓታልና ነው (ችግሩ ከደረሰባት በኋላ ሳይሆን ሳይደርስ በፊት) በመሆኑም ይሄን ያደረገላት አምላኳ መድኃኒቷ ነውና ይሄንን ታላቅ ሥራ ሠርቶላታልና ያዳናትን አምላኳን መድኃኒቴ አለችው፡፡ እነዚህ ወገኖች ሌላው ያልተረዱት ነገር ቢኖር እሷን ጥንተ አብሶ አለባት ሲሉ ልጇንም የለበሰው ሥጋ የሷን እንደመሆኑ እሱንም አለበት እያሉት መሆናቸውን ነው፡፡ ይሄንን ያህል የማያስተውሉ ናቸው አይ እሱማ የለበትም ካሉ የለበሰው ሥጋ እኮ የድንግል ማርያም እንጅ ከሰማይ ይዞት የመጣ አይደለም እንዴትና መቸ ነው ላይኖርበት የቻለው? ለሚለው ጥያቄ መልስ መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ "የክርስቶስ ሞት ለድንግል ማርያም ያስፈልጋታል ወይስ አያስፈልጋትም?" የሚል ጥያቄ ይነሣል፡፡ ልብ ካልነው የላይኛውን ጥያቄ ስንመልስ እኮ አብሮ ተመልሷል፡፡ ግልጽ ለማድረግ እንደሚታወቀው ከክርስቶስ ሞት በፊት ጻድቁም ኃጥኡም ሲሞት ሲያል መግባቱ ግድ ሆኖ የነበረበት ብቸኛው ምክንያት ጥንተአብሶ ነበር፡፡

ክርስቶስ ወደዚህ ምድር የመጣውም ይሄንን ዕዳ በደል ለመደምሰስ ነው፡፡ በመሆኑም ክርስቶስ ከመወለዱ በፊት ወላዲተ አምላክን ከዚህ ዕዳ ነጻ አድርጓታልና የክርስቶስ ሞት ከወላዲተ አምላክ ውጭ ላለነው የአዳም ልጆች ሁሉ እንጅ ለቅድስት ድንግል ማርያምማ አያስፈልጋትም ማለት ነው፡፡ የአዳምን በደል ከመደምሰሱ በፊት በተለየ ሁኔታ ለራሱ ሲል እሷን አንጽቷታልና፡፡ በጥቅሉ ግን የክርስቶስ ሞት ለሰው ልጆች ሁሉ ነውና ይሄንን የማዳን ሥራ ለመሥራት ሲል ነውና እሷንም ሳታድፍ በፊት ሊያነጻት የቻለው እሱ ሰው ሆኖ ለመሞት ባይመጣ ኖሮ አያነጻትም ነበርና ሰው ሆኖ ሞቶ ሊያድነን ስለወደደ ነውና ያነጻት ያዳናት የታደጋት በዚህ ምክንያት የክርስቶስ ሞት ለእሷም ጠቅሟታል ድኅነት ሆኗታል ማለት ይቻላል፡፡

እግዚአብሔርን እንደ እግዚአብሔርነቱ የሚያውቅ፣ የሚያምን የሚረዳ ማለትም ከስፋቱ እስከ ጥልቀቱ፣ ከግዝፈቱ እስከ ርቀቱ እንዲህ ነው ብለን ልንገልጸው የማንችለውን ይህንን የምናየውና የማናየው የምናውቀውና የማናውቀው

ዓለማት ሁሉ የእጁ ሥራ የሆነ በመዳፉ የተያዘ ወይም የፈጠረና ፈጥሮ የሚገዛ፣ ለኃያልነቱ ምሳሌ የሌለው ቃል የማይገልጸውን፣ እንዲህ ነው ተብሎ ሊነገር ሊገለጽ የማይቻል፣ ጅማሬና ፍጻሜ የሌለው፣ ፍጹም ገናና፣ ፍጹም ክቡር፣ ፍጹም ንጹሕ፤ ለኃይላት፣ ለሥልጣናት፣ ለመናፍስትም ፍጹም አስፈሪና አስደንጋጭ የሆነ አምላክ መሆኑን የሚያውቅ፣ የሚያምንና የሚረዳ ክርስቲያናዊ ልቦና ወይም ኅሊና ያለው ሰውና ይህም አምላክ ከቅድስት ድንግል ማርያም እንደተወለደ የሚያምን የሚቀበል ሰው ለእርሱ ማደሪያነት ወይም እሱን ለመውለድ የምትገባው ሴት ደግሞ ምን ያህል የንጽሕናዋ ነገር ሊናገሩት የማይቻል፣ ቅድስናዋ ወደር የሌለው ልትሆን እንደምትችል ወይም እንደሚገባትና እርሱ እራሱም ለመለኮታዊ ክብሩና ንጽሕናው ሲል በዚህ ደረጃ እንደሚያዘጋጃት ምንም ዓይነት ምስክር ሳያሻው ከቅን፣ ትሑት፣ ንጹሕና ጻድቅ ልቦናው ተረድቶ ያምናል ይቀበላል፡፡

እመቤታችንን በጥንተ አብሶ ወይም በውርስ ኃጢአት የሚጠረጥር ሰው በእርግጠኝነት እግዚአብሔርን እንደ እግዚአብሔርነቱ አያውቀውም አያምነውምም፡፡ በመሆኑም በውጭ ካሉት መናፍቃን እስከ ውስጥ ካሉት ከሐዲያን ልብሳቸውና ቆባቸው እንጂ ልባቸው ክርስቲያን ያልሆነ ያልጸጸሰ ወይም ያልመነኮሰ፣ ቆዳቸው እንጂ ልባቸው ያልተቀባ፣ ሳይጠሩ የመጡ፣ ሰይጣን ለተልእኮው ያስገባቸው፣ የዲያብሎስ የግብር ልጆች እንደሆኑ ቅዱሱ ሐዋርያ ዮሐንስ በራዕዩ ተናግሯል "እግዚአብሔርንም ለመሳደብ፣ ስሙንና ማደሪያውንም፣ በሰማይ የሚያድሩትን ሊሳደብ አፉን ከፈተ" ራዕ.13፥6

"ዘንዶውም ወደ ምድር እንደ ተጣለ ባየ ጊዜ ወንድ ልጅ የወለደችውን ሴት አሳደዳት ከእባቡም ፊት ርቃ አንድ ዘመን ዘመናትም የዘመንም እኩሌታ ወደ ምትመገብበት ወደ ሥፍራዋ ወደ በረሀ እንድትበር ለሴቲቱ ሁለት የታላቁ ንሥር ክንፎች ተሰጣት፤ እባቡም ሴቲቱ በወንዝ እንድትወሰድ ሊያደርግ ወንዝ የሚያህልን ውኃ ከአፉ በስተኋላዋ አፈሰሰ፡፡

ምድሪቱም ሴቲቱን እረዳቻት፤ ምድሪቱም አፏን ከፍታ ዘንዶው ከአፉ ያፈሰሰውን ወንዝ ዋጠችው ዘንዶውም በሴቲቱ ላይ ተቆጥቶ የእግዚብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁትን፣ የኢየሱስም ምስክር ያላቸውን፣ ከዘርዋ የቀሩትን ሊዋጋ ሔደ፡፡ በባሕርም አሸዋ ላይ ቆመ" ዮሐ. ራእ 12÷13-18 ክርስቲያኖችና መናፍቃንም ይህ ጥቅስ ለማን አንደተነገረ ያለ ልዩነት ይስማማሉ ወይም ስለ ወላዲተ አምላክና ስለ አማኑኤል እንደሆነ ያምናሉና የሚያነታርከን ነገር አይኖርም ማለት ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ዘንዳ የጥቅሱን ትርጉም በስሱ እንይ፡-

ዘንዶ የተባለው በጊዜው አንድ ልጇን ሊገልባት ሲያሳድዳት የነበረው ሄሮድስ ሲሆን ፍጻሜው ግን በሰው ልጆች ልቦና ላይ እንክርዳድ ወይም ክሕደት ኑፋቄ የሚዘራ ዲያብሎስ ነው፡፡ "እባቡም ሴቲቱ በወንዝ እንድትወሰድ ሊያደርግ ወንዝ የሚያህልን ውኃ ከአፉ በስተኋላዋ አፈሰሰ" ይህም ማለት በጊዜው ድንግል ልጇን ሰይጣን ካደረበት

ከሄሮድስ ሥይፍ ለማትረፍ በረሃውን አቋረጣ ወደ ግብጽ በተሰደደች ጊዜ ሰይጣን አድሮበት የሚያሠራው ሄሮድስ ያደረሰባትን መከራ ሲናገር ነው፡፡

ፍጻሜው ግን እባቡም ወይም ዘንዶውም ሴቲቱ በወንዝ እንድትወሰድ ሊያደርግ ወንዝ የሚያህልን ውኃ ከአፉ በስተኋላዋ አፈሰሰ ማለት ዲያብሎስ በመናፍቃን አንደበት አድሮ በቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም ላይ የክህደት፣ የኑፋቄ፣ የንቀት፣ የዘለፋና የስድብ ቃልን አፈሰሰ አወጣ ተናገረ ማለት ነው፡፡

"ምድሪቱም ሴቲቱን እረዳቻት ምድሪቱም አፍዋን ከፍታ ዘንዶው ከአፉ ያፈሰሰውን ወንዝ ዋጠችው" በጊዜው ሄሮድስ ሕፃኑን ይዞ ለመግደል ያሳድዷት የነበሩትን የሄሮድስን ሠራዊት እርሷን ለመያዝ በሚያሳድዷት ጊዜ ግዑዛን ሣር ቅጠሉ ሁሉ ለፈጣሪው ለአማኑኤልና ለእናቱ ተገን ከለላ እንደሆነ፤ ለሄሮድስ ሠራዊት ግን እሾሁ አሜኬላው ጣርና ጋር እንዳበዛባቸውና ከዚህም የተነሣ ሊይዟቸው እንዳልቻሉ ሲናገር ሲሆን ፍጻሜው ደግሞ "ምድሪቱም ሴቲቱን እረዳቻት አፍዋን ከፍታ ዘንዶው ከአፉ ያፈሰሰውን ወንዝ ዋጠችው" ማለት ምድር የተባለው የሰው ልጆችን ማለትም ምዕመናንን ነው፡፡ ዘንዶው በመናፍቃን ልቦናና አንደበት አድሮ የሚያፈሰውን የስድብ፣ የዘለፋ፣ የክሕደትና የኑፋቄ ቃል ምዕመናን ሰምተው እንዳልሰሙ በልቦናቸው ሳያሳድሩ ንቀው በማለፍና በኑፋቄው ባለመሰናከል ባለመውደቅና ባለመመረዝ ቅድስት ድንግል ማርያምን የሚገባትን ያህል ክብር በመስጠት የዘንዶውን ድካም ከንቱ ያደርጋሉና ነው፡፡

"ዘንዶውም በሴቲቱ ላይ ተቆጥቶ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁትን፣ የኢየሱስም ምስክር ያላቸውን፣ ከዘርዋ የቀሩትን ሊዋጋ ሔደ በባሕርም አሸዋ ላይ ቆመ" ዘንዶውም በሴቲቱ ላይ ተቆጥቶ ማለት ድንግል ከአምላክ በተሰጣት የማማለድ፣ የማስታረቅ፣ የመራዳት ጸጋና በረከት በልጇ ስም አምነው የተጠመቁትን ክርስቲያኖችን ወይም ምእመናንን ትራዳለችና፣ ትደግፋለችና፣ ታነሣለችና፡፡ በዚህ አገልግሎቷ ዲያብሎስ ተቆጥቶ "የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁትን" አለ፤ የአንዲቱ ቤተ ክርስቲያን ልጆች ዐሥርቱ ትእዛዛትን፣ ስድስቱ ቃላተ ወንጌልን ሳይለዩ ሳይነጥሉ ይጠብቃሉና፤ "የጌታ ኢየሱስም ምስክር ያላቸውን" አለ፤ "በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ! የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም፡፡ በዚያ ቀን ብዙዎች ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ! በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን በስምህ ብዙ ተአምራትን አላደረግንምን ይሉኛል፡፡ የዚያን ጊዜም ከቶ አላውቃችሁም እናንተ ዓመፀኞች ከእኔ ራቁ ብየ እመሰክርባቸዋለሁ" አለ ጌታ በወንጌል ማቴ.7፥21-23፡፡

ስሙን ከጠሩ ከዚያም አልፈው በስሙ ተአምራትን የሚያደርጉትን እንዴት አላውቃቹህም ይላቸዋል? ያልን እንደሆነ ዛሬ ክርስትና ሃይማኖት ነኝ የሚለው ቁጥሩ ከ 30 ሽህ ካለፈ ቆይቷል ይሄ ሁሉ ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ! ባይ ነው፡፡ ከዚህ ሁሉ ሃይማኖት ነኝ ባይ ግን ክርስቶስ ኢየሱስን በትክክለኛ ማንነቱ የምታምን የምትገልጽ የምትመሰክር አንዲቷ ብቻ

ናት ፡፡ ቃሉም የሚለው "አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት አንድ ጌታ" በመሆኑ ኤፌ.4፣5, ይሁ. 1፤3 ስለሆነም የተቀሩት ሁሉ የሚጠሯቸውና የሚሰብኳቸው የሚያምኑባቸውም ኢየሱሶች ሐሰተኞች ኢየሱሶችን ወይም ክርስቶሶችን ማቴ.24፣24

ኢየሱስ ነኝ ብሎ የሚመጣውን አውሬውን ነው፡፡ ሰይጣንም ለክፋቱ ለተንኮሉ ለዓላማው በእነኝህ ሐሰተኞች ክርስቶሶች ስም ተአምራትን ያሠራቸዋል፡፡ በመሆኑም ነው የድንግል ልጅ መድኃኔዓለም ክርስቶስ ቅዱስ ቃሉ "የጌታን ስም የጠራ ሁሉ ይድናል!" ሐዋ. 2፤21 ሮሜ 10፤13 ብሎ እያለ "ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ! በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን ፣በስምህ አጋንንትን አላወጣንምን?፣ በስምህ ብዙ ተአምራትን አላደረግንምን?" ሲሉት "ከቶ አላውቃቹህም እናንት ዓመፀኞች ከእኔ ራቁ!" ብሎ የሚመሰክርባቸው፡፡

"በስምህ" አሉ አለ እንጅ በስሜ አለማለቱን ልብ ይሏል፡፡ ዘንዶው የተቆጣው በሴቲቱ ላይ ነውና የሚዋጋውም ቃሉ እንዳለው "የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁትን፣ የኢየሱስም ምስክር ያላቸውን፣ ከዘርዋ የቀሩትን" ነውና "ከዘርዋ የቀሩትን" አለ የወላዲተ አምላክ የሥጋ ዘመድ የሆኑትን ማለት ሳይሆን የጌታችንን የአምላካችንን የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን በሐዋርያው ዮሐንስ አማካኝነት ለክርስቲያኖች ሁሉ ከጌታ ለእኛ እናትነት የተሰጠችን የመስቀሉ ሥር የእናትነት ስጦታና በልጅነታችንም እንንከባከባት እንጠብቃትም ዘንድ የጣለብንን የአደራ ቃል ተቀብለን ወላዲተ አምላክን እናታችን ያደረግንና የእናትነት አገልግሎቷን የምናገኘውን እሷም ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስ በወንጌላዊው ዮሐንስ እማካኝነት "እነሆ ልጅሽ" በሚለው አምላካዊ ቃል በተሰጣት የእናትነት አደራ "ልጆቸ" የምትለንን እንደ ልጅ የምትንከባከበንን የምታገለግለንን ማለቱ ነው "ከዘርዋ የቀሩትን" ሲል፡፡ እንደሚታወቀው ልጅነት ወይም የክርስቶስ ወገንነት የሚኮነው የሚገኘው በዘር ኃረግ ሳይሆን እሱን በማመን የሚገኝ ነውና፡፡

በመሆኑም ወላዲተ አምላክን ልጇ በሰጠን እናትነቷ ትምክህታችን ያደረግንና ንጽሕናዋን ቅድስናዋን የምናውቀውን የምናምነውን "እናታችን" የምንላትን የአንዲቱን ቤተ ክርስቲያን የተዋሕዶ ልጆችን (የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት የሚጠብቁትን ፣ የኢየሱስም ምስክር ያላቸውን፣ ከዘሯ የቀሩትን) ተብሎ የተነገረልን የዚህች ቤተክርስቲያን ልጆችን ብቻ ነው፡፡ "ያለ ወላዲተ አምላክ አማላጅነት ዓለም አይድንም" ይሉሀል ይሄ ነው፡፡ እሷ ሌላ በር ሌላ አዳኝ ትሆናለች ማለት ሳይሆን በልጇ በርነት በልጇ አዳኝነት ነው የምታድነው፡፡ መዳን በሌላ በማንም የለምና፡፡

ይህ የባሕታውያን አባባል የዓለም ድኅነት በክርስቶስ ኢየሱስ መፈጸሙን የሚቃረን አባባል የሚመስላቸው ሰዎች ጥቂቶች አይደሉም፡፡ የዓለም ድኅነት የተፈጸመው በክርስቶስ ኢየሱስ ደም ነው፡፡ ይህ ድኅነት ነግሥብን ከነበረው ሞት ማለትም ከጥንተ አብሶ ወይም ከውርስ ኃጢአት ደዌ መፈወስ ነጻ መውጣት ነው፡፡ ዓለም ከዚህ የሞት ቀንበር በክርስቶስ ደም ነጻ ቢወጣም ቢድንም ቢፈወስም ሕግን ትዕዛዝን ቃልን በመተላለፍ፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ባለመፈጸም፣ ለሥጋ

ምኞት በመውደቅ በመገዛት ከሕግ በታች ሆኗል ኃጢአት ሠልጥኖበታል ረክሷል “ጻድቅ የለም አንድስ እንኳ፣ ኃጢአት የለብኝም የሚል ቢኖር እራሱን ሐሰተኛ ያደርጋል” እንዲል ቃሉ፡፡

እንግዲህ ዓለም ክፋትን ጥፋትን በመምረጡ በኃጢአት ከረከሰ ለመጽደቅ ይቅር መባል ምሕረት ማግኘት ይጠበቅበታል፡፡ ጌታ በወንጌለ ሉቃ. 16፤19-31 ላይ የአብርሃምን የአልአዛርንና የባለጸጋውን የነዌን ታሪክ አንሥቶ እንደተናገረው ቅዱሳን ከሞቱም በኋላ እንዲያማልዱ የሚጠየቁ የሚለመኑ ከሆነና ሲፈቅዱ የሚያደርጉት ካልፈቀዱ የሚከለክሉት ነገር ካለ፤ በዮሐንስ ራእይ 6፤9-11 ላይ በሔሮድስ ግፍ ተፈጽሞባቸው የተፈጁት 144,000 ሕፃናት አድርገውት እንደተገለጸው ጻድቃን ወይም ቅዱሳን ከሞቱም በኋላ ፍላጎታቸው እንዲፈጸም እግዚአብሔርን የሚለምኑ የሚማልዱና ፍላጎታቸውንም የሚያስፈጽሙ ከሆነ፤ ከምልጃዎች ሁሉ የሚበረታውና ዓለምን የማዳን አቅም ያለው ምልጃ ልመና የወላዲተ አምላክ ምልጃ ወይም ልመና ነው፡፡

ምክንያቱም ባለ ሠላሳው የባለ ስልሳውን ያህል ባለ ስልሳውም የባለ መቶውን ያህል የማማለድ የማስማር አቅምና ፈቃድ የለውምና፡፡ ወላዲተ አምላክ ግን ያላት ዋጋ ከባለ መቶዎችም በላይ እጅግ የላቀ ነውና በእግዚአብሔር ፊት ከእርሷ የከበረ የለምና፣ መትሕተ ፈጣሪ መልዕልተ ፍጡራን ናትና በዚህም ምክንያት ምልጃዋ ለዓለም የሚበቃው የእርሷ ምልጃ ነው፡፡ “ያለ ወላዲተ አምላክ አማላጅነት ዓለም አይድንም!” የሚለው የባሕታዊያኑ ቃል መግለጽ የፈለገው ይሄንን ነው ሌላ አይደለም፡፡ ዓለም ሁሉ በምልጃ በልመና ይዳን ከተባለ ለዓለም የሚበቃው ምልጃ ወይም ልመና የእሷ ነው ለማለት ነው፡፡ ይህም እውነት ነው፡፡

ይህ አባባል ቀደም ሲል ከራእዩ ዮሐንስ ጥቅስ ጠቅሰን በቀረበው የቅዱስ ቃሉን ትርጓሜ ለማስረዳት እንደተሞከረው የኢየሱስን የእናትነት ስጦታ ተቀብሎ ልጇ ሆኖ ከዘሯ ያልተቆጠረ የኢየሱስ ምስክር የለውምና፣ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ የሚጠብቅ አይደለምና የመዳን ተስፋ የለውም፡፡ ልጆቿ የሆኑትን ግን ዲያብሎስ እነሱን “…ሊዋጋ ሔደ በባሕርም አሸዋ ላይ ቆመ!” አለ፡፡

አሸዋ በእምነት ያልጸና የተጠራጣሪና የከሐዲ ልብ ምሳሌ ነው፡፡ “ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው ሁሉ ቤቱን በዓላት ላይ የሠራ ልባም ሰውን ይመስላል፡፡ ዝናብም ወረደ ጎርፍም መጣ ነፋስም ነፈሰ ያንም ቤት ገፋው በዓለት ላይም ስለተመሠረተ አልወደቀም፡፡ ይህንም ቃሌን ሰምቶ የማያደርገው ሰው ሁሉ ቤቱን በአሸዋ ላይ የሠራ ሰነፍ ሰውን ይመስላል፡፡ ዝናብም ወረደ ጎርፍም መጣ ነፋስም ነፈሰ (ሰውን ከእግዚአብሔር የሚለዩ ፈተናዎች ኑፋቄ ክህደት መከራ ደረሰበት) ያንም ቤት መታው ወደቀም አወዳደቁም ታላቅ ሆነ (በእምነት የጸና አይደለምና ኑፋቄ ክሕደት አለበትና ወደቀ አወዳደቁም የከፋ ሆነ) ማቴ.7፥24-27

በመሆኑም በባሕር አሸዋ ላይ ቆመ አለ፤ በመናፍቃን ልቦናና አንደበት ላይ አደረ ክርስቲያኖችን ያሳድድ፣ ይዋጋ፣ መከራም ያደርስባቸው ዘንድ ማለቱ ነው፡፡ የሚከበሉት መከራ ግን ለክብር የሚያበቃቸው ነውና የሚጠቀሙበት እንጅ የሚጎዱበት አይደለምና የሚያስከፋ አይሆንም፡፡ እናም ክርስቲያኖች ይህ ወላዲተ አምላክን በጥንተ አብሶ ወይም በውርስ ኃጢአት የመጠርጠር ኑፋቄ ምን ያህል ከባድና አጋንንታዊ መሆኑን የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ከሐዋርያት ባገኘችው ትምህርት አረጋግጣለችና በዚህ ጉዳይ ላይ ምንም ዓይነት ብዥታ የለባትም፡፡

በሚያሳዝን ሁኔታ ግን ከኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ጋራ አንድ ዓይነት ዶግማ (አምደ እምነት) እና ቀኖና (ሥርዓት) የነበራቸው አኃት አብያተክርስቲያናት የምንላቸው የግብጽ፣ የሶሪያ፣ የአርመንና የሕንድ አብያተክርስቲያናት አውሬው ዘንዶው ባሰማራቸው አገልጋዮቹ (በተሐድሶ መናፍቃን) ውጊያ ዘመቻ ተሸንፈው ከዘንዶው አፍ በሚፈሰው ኑፋቄ ተመርዘው የቀድሞውን አስተምህሮዋቸውን በመተው እመቤታችንን "ጥንተ አብሶ አለባት!" በማለት መሸነፋቸውን መውደቃቸውን አረጋግጠዋል፡፡ አብያተ ክርስቲያናቱ በይፋ አቋማቸው እምነታቸው ይህ እንደሆነ ይግለጹ እንጅ ከመሀከላቸው ግን አሁንም ድረስ የቀድሞውን አስተምህሮ ያያዙ ከጳጳሳት እስከ ምእመናን ድረስ እንዳሉ ይነገራል፡፡

ከዘንዶው አፍ በሚፈሰው ኑፋቄ እንዳንመረዝ የወላዲተ አምላክ ረድኤት የልጇ ጥበቃ አይለየን አሜን፡፡ ይቆየን

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ወለወላዲቱ ድንግል ወለ መስቀሉ ክቡር አሜን!!

ይህ ጽሑፍ ከዓመታት በፊት በአንድ የቤተክርስቲያን ጉዳዮችና ትምህርቶች በሚስተናገዱበት ድረገጽ ተለጥፎ የነበረ ጽሑፌ ነው፡፡ ከዚያ አንሥተው በመጽሐፍ አሳትመው የሸጡ ወገኖች መኖራቸውን መጠቆም እወዳለሁ፡፡

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው

amsalugkidan@gmail.com

*http://www.ethiopanorama.com*